የሰበር መ/ቁጥር 29005

ሚያዝያ 14 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት

**ተጠሪዎች፡-** 1. ግርማቸው ይላላ ቀረበ፡፡

2. አዲስ አበባ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ባለስልጣን

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የግንባታ ፈቃድ እና ካርታ ይሰጠኝ በሚል 1ኛ ተጠሪ ያቀረበውን ክስ መሠረት ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪው ክስ የመሠረተው በ2ኛው ተጠሪ ላይ ነበር፡፡ ክሱ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም በሁለቱ መካከል የተሰማውን ክርክር ከመረመረ በኋላ፣ 2ኛ ተጠሪ የተጠየቀውን የግንባታ ፈቃድ እና ካርታ ለ1ኛ ተጠሪ ይስጥ በማለት ውሣኔ ሰጥቶአል፡፡ የአሁኑ አመልካች ክርክሩ የእኔን መብት የሚነካ ነው በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ሕግ ቁጥር 358 መሠረት መቃወሚያ ያቀረበው ከዚህ በኋላ ነው፡፡ ፍ/ቤቱም መቃወሚያውን የተመለከተ ቢሆንም፤ በመጨረሻ ግን ተቃዋሚው /የአሁኑ አመልካች/ ተጠሪነቱ ለ2ኛ ተጠሪ በመሆኑ ቀደም ሲል በተደረገው ክርክር ተካፋይ አልነበረም የሚባል አይደለም የሚል ምክንያት በመስጠት መቃወሚያውን ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔውን አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች የካቲት 14 ቀን 1999 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረ 378 ዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 መሠረት ያቀረበው መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ፣ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው አመልካች በአቃቂ ክፍለ ከተማ ስር የተደራጀ አስፈፃሚ አካል ነው፡፡ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 10/2/ እንደተመለከተው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ያሉት ክፍለ ከተሞች የየራሳቸው ምክር ቤት፣ ዋና አስፈፃሚ እና ቋሚ ኮሚቴ ኖሯቸው የተደራጁ ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው አካላት ናቸው፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 30 እንደተደነገገውም ክፍለ ከተሞች ባልተማከለ የስልጣን ክፍፍል መርህ በተሰጠው የቦታ ክልል ማዘጋጃ ቤት በመሆንና ከከተማው

